ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 9 ቁጥር 3 የካቲት 11 ቀን 2014 ዓ.ም.

# የካቲት ሕዝባዊ አብዮት

ታላቁ የኢትዮጵያ አብዮት እዮቤልዩ ዕድሜውን ሊደፍን ሁለት ዓመት የቀረው ሲሆን በዘንድሮው የካቲት ወር የዛን የየካቲቱን 66 ሕዝባዊ አብዮት አርባ ስምንተኛ ዓመት የ"ያ ትውልድ ተቋም" ሊዘክረውና ከትውልድ ትውልድ ሊያሻግረው ይወዳል። የዛሬ 48 ዓመት የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢ.መ.ማ) ጠሪነት የተደረገውን የሥራ ማቆም አድማ አስከትሎ የተቀጣጠለው የየካቲት 1966 ዓ.ም. አብዮት በውስጡ ግዙፍ ትርጉም ይዟል። የመምህራን ሥራ የማቆም አድማ አመጣጥና ክንውን በወቅቱ በነበሩት መሪ መምህራን ጠንሳሽነት ብቻ የተነሳ አልነበረም። ከ1953 ዓ.ም. በተለምዶ "ታህሳስ ግርግር" እየተባለ በሚጠቀሰው መፈንቅለ መንግሥት በቀጣይነት እየተቀጣጠለ የመጣውና ህገራዊ መልክ እየያዘ የተጓዘው የተማሪው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለየካቲቱ አብዮት የራሱ የሆነ ከፍተኛ ድርሻ ተጫውቷል። ያም ሆኖ ተማሪ ብቻውን ያመጣው እምቢተኝነት ለማለት ባያስደፍርም በስተመጨረሻ በአብዮቱ መባቻ ሁሉም ሰራተኛ፤ ላብ አደር፤ አፈር ገፊና ወታደር ሳይቀር የተካፈለበት እንቅስቃሴና አመጽ ነበር፤ የየካቲቱ አብዮት።

የሠራዊቱ ዝቅተኛ የደሞዝ ሁኔታ፣ አርሶ አደሩ ላይ የሚደርሰው ባላባታዊ ግፍና እንግልት፣ የሠራተኛው ክፍል ከእጅ ወደ አፍ የኑሮ ውጥረት፣ ወጣቱ በአግባቡ እንዳይማር አሰናክሎ ሊያስቀር የታቀደው በወቅቱ አገላለጽ "ሴክተር ሪቪው" የትምህርት ፖሊሲ፣ የሃይማኖት ልዩነትን ለማስተካከል ትኩረት አለመስጠት፣ በሴቶች ላይ የሚደርሰው ፆታዊ በደልና ልዩነት ሌላም ሌላ ተደማምረው ነው የካቲት 1966 እንቅስቃሴን የወለዱት። የየካቲት 1966 እንቅስቃሴ ይዟቸው የተነሳው ጥያቄዎች ተያያዥነት፣ የአንዱ በደል የሌላውም የመሆኑ ትስሥር ጥያቄያችሁ ጥያቄያችን፣ ብሶታችሁ ብሶታችን፣ ትግላችሁ ትግላችን ስሜትን አላብሶና ህገራዊ ይዘትን ተከናንቦ የሁሉም ነዋሪ፣ የሁሉም ሃይማኖት፣ የሁሉም ፆታ፣ የሁሉም እድሜ ክልል ጥያቄ እና እንቅስቃሴ በመሆኑ ነው የካቲት ሕዝባዊ አብዮት የሚባለው።

የየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እጅግ ጉልህ ሚና የሚይዘው በወቅቱ የተነሱት ጥያቄዎች የሥርዓት ለውጥ በማምጣታቸው ነው። ለሦስት ሺህ ዓመት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ንጉሣዊ አስተዳደር ዓፄ ኃይለሥላሴ ላይ እንዲያከትም አድርጎታል። በአርሶ አደሩና (ቀደም ሲል በነበረው አጠራር በጭሰኛውና) በባላባቱ፣ በባለ እርስትና በጉልተኛው መካከል የነበረውን የገዥ ተገዥ ሠንሰለት የየካቲት 25 ቀን 1967 ዓ.ም. አዋጅ በጣጥሶታል። የየካቲት 1966 እንቅስቃሴ እኩልነትን እና ሶሻሊዝምን ሲያዘምር "የዓለም ተጨባጭ እና ነባራዊ እውነታ ምን ነበር?" ብሎ መጠየቅ አግባብነት እንዳለው እናስምርበታለን። የዓለም ሃያላን ሀገሮች በተለይ አፍሪካን ተቀራምተው በቅኝ አገዛዝ ወጥመድ ያስገቡበት ዘመን እንዲወገዝና አፍሪካ ነጻነቷን እንድትቀዳጅ

የእነ ቼ ጉቬራ "ፋኖ ተሰማራ!" ርዕዮተ-ዓለም ዛሬም ባልጠገቡት ሃያላን ሀገሮች በወቅቱ አጠራር "ኢምፔሪያሊዝም" ላይ የተወረወረ በትር ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ሀገራችን ስንመጣ ክብር ለዓፄ ምኒልክና ለሕዝባችን የዐድዋ ድል ለአፍሪካ ነፃ መውጣት ከሶሻሊዝም ርዕዮተ-ዓለም በላቀ ከተራራው ጫፍ ይቀመጣል። የዚህ የቅኝ አገዛዝ እና የወቅቱ ሃያላን መንግሥታት የእርስ በርስ ፍልሚያ ዓለም በሁለት ርዕዮተ-ዓለም ጎራ ውስጥ እንድትሰለፍ አድርጓታል፤ "ሶሻሊዝም" በአንድ በኩል "ካፒታሊዝም" በሌላ በኩል። ይህን የዓለማችንን ነባራዊ ሁኔታ ተንተርሶ ስለ የካቲት 1966 እንቅስቃሴ ትንታኔ ሲሰጥ በጊዜው "ምን መደረግ ነበረበት?" የሚለውን ምላሽ ለመስጠት መድፈርን ይጠይቃል።

የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታም ስንቃኝ ዓፄ ምኒልክ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሉዓላዊነቷን፣ ክብሯን፣ ነፃነቷን እጅግ አንጸባራቂ በሆነው የዐድዋ ድል ኢትዮጵያችንን ከፍ አድርገው ብቸኛዋ የመንግስታት ህብረት (League of Nations) መስራች እንድትሆን ያበረከቱት አስተዋጽዖ እንደተጠበቀ ሀገራችን በዓፄ ኃ/ሥላሴ ዘመን ይህን ድሏን ተጠቅማበታለችን? ለሚለው ምላሽ ስጪ እንኳን ያኔ ዛሬ እንደማይገኝ መናገር ይቻላል። ምላሻችን የካቲት 1966 አብዮትን ለማናናቅ ከሆነ እጅግ ቀላል ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን በለስ የቀናቸው የዘር ድርጅቶች ዘረኝነትን በተኑብንና ትንታኔ ያቃታቸው አንዳንድ ምሁሮች የካቲት 1966 ሕዝባዊ እንቅስቃሴን ከዚህ ጋር ለማያያዝ ቢጥሩ ሳያውቁት ቀርቶ ሳይሆን ታሪክን ለማጠማዘዝ ካላቸው ፍላጎት ወይም "ትምህርት ቤት ሄዱ እንጂ ያልተማሩ ተንታኞች" ብንላቸው ያንሳቸዋል።

"ያ ትውልድ ተቋም" የካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮትና መሰል ታሪካዊ ወቅቶችን በየዓመቱ ስንዘክር ሳይታወስ እንዲያልፍ ፍላጎት ያላቸውን ወይም ታሪኩ ላይ ጥላሸት እየቀቡ ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚጥሩትን ከመከላከል በዘለለ ይህም ነበር ማለት ይገባናልና ነው። በተጨማሪም የምንዘክራቸው የያ ትውልድ ቀናት በውስጣቸው በርካታ ሰማዕታት፣ ንጹሃን ሙታን፣ በሙቶ ሺህ የሚቆጠር ቤተሰቦችን፣ ክልል ያለየት ሀገርን፣ ኢትዮጵያዊነትን ያነገበ ትውልድን፣ ሃይማኖት ያልከፈለውን እምነትን ይይዛልና ይህ ነበር ትውልዳችን ብለን ለመመስከር እንገደዳለን።

ዛሬ ሀገራችን ከተዘፈቀችበት ዘረኝነት አንፃር ስንቃኘው አዎ ከየካቲት 1966 ዓ.ም. በፊትም የፖለቲካ ድርጅቶች መኖራቸውን በጥቂቱም ሻቢያ፣ ኦነግ፣ ሲሕን (ሲዳማ ሕዝብ ንቅናቄ)፣ ኦጋዴን ነጻ አውጭ ንቅናቄ (ኦነአን) መች ተመሰረቱ ብሎ ማገናዘብ ታሪክ ተንታኞችን ይመለከታል። የካቲት ይዟቸው የተነሳው ሕዝባዊ መፈክሮች በዋነኝነት "መሬት ለአራሹ" "ትምህርት ለሁሉም" "የዴሞክራሲ መብቶች ያለገደብ ይከበሩ" "ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት አሁኑኑ" ሲሆኑ እነዚህን አያይዞ የሃይማኖት፣ የፆታ እና የብሔር እኩልነትን አንስቷል። "የምሁር ለቅሶ መልሶ መላልሶ" ስለሆነብን ለተተኪው ትውልድ ስንል መደጋገም ያለብን የሃይማኖት እኩልነት ስንል አንዱ ሃይማኖት ከሌላው እኩል በሕዝብና በመንግስት ዘንድ፣ ሁሉም እንደእምነታቸው ከመንግስትና ፖለቲካ ነጻ ሁነው ይስተናገዱ ማለታችን ነው፤ አንዱ ሌላውን የበታች አያድርግ ነው። የሴቶች እኩልነት ሲጠየቅ ትላንት ሴቶች በወንዶች የበላይነት ተጨቁነዋልና ተራቸውን ይጨቁኑ ሳይሆን በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማህበራዊ ህይወት እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከፍ የተደረገ መፈክር ነው። የብሔር/ብሔረሰቦች መብት ይከበር ሲባል በኢትዮጵያ የአንድ ብሔር የበላይነት ነበር በሚል የተዛባ አስተሳሰብ ያንን ብሔር ደምስሰን ሌላ ብሔር አንግሰን ሀገሪቷን በዘርና ቋንቋ እንከፋፍል በሚል እሳቤ እንዳልነበር በጽሁፍ ያሉ የያ ትውልድ መረጃዎች እያው ምስክር ናቸው።

የካቲት 1966 ዓ.ም. የተነሳው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በውስጡ በርካታ ሀገሬን፣ ኢትዮጵያዬን ባይ እንዳባቀለ ሁሉ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ለዛሬ የዘረኝነት እቅዳቸው ከሃምሳ ዓመት በፊት

ለኢትዮጵያ "የመቶ ዓመት የቤት ሥራ" ለመስጠት ከባዕዳን ኃይሎች ጋር የዶለቱ እንደነበሩ ለመመርመር ያመች ዘንድ "ያ ትውልድ ተቋም" ያከማቻቸውን መረጃዎች መመልከት እና ቅንነትም ካለ በጎደሉት መሙላት ለተሰሩት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ኩነቶች ለትውልድ ይጠቅማልና እኛ ሳንሸማቀቅ ይህ ነው ታሪካችን ስንል የሌሎችንም በማካተት ነው።

በየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት የተደራጀ የፖለቲካ ሀይል ባለመኖሩ አንዳንድ ቅንና ሀገር ወዳድ የወታደሩ የሹማምንት ለስልጣን ቢበቁም፤ ጥቂቶቹ ግን፤ ኢትዮጵያችን ለልጆቿ አልታደለችምና ፋሺስት መንግሥቱ ኃይለማርያምን እና መሰሎቹን አብቅላ የደም መሬት ለመሆን በቅታለች። በመንግስቱ ኃ/ማርያም የሚመራው ደርግ የሰብአዊ መብቶችን በመጣስና የዴሞክራሲያ መብቶችን በመግፈፍ፣ ስልሳ የሚሆኑ የቀድሞ ባለስልጣኖችን በግፍ በመግደል ነበር አብዮቱ የተነሳለትን ዓላማ አስቶ የአምባገነን መንግስት መመስረቱን ያሳወቀው። ያም ሲሆን አንዳንድ የዛን ዘምን ምሁራን "ሂሳዊ ድጋፍ" እንሰጣለን በሚል ከደርግ ጎን ተሰልፈው የጥፋቱ አራማጅ እንደነበሩ ታሪክ ምስክር ነው።

የየካቲት 66 ዓ.ም. ዘረኝነትንና የዘር ክልልን በኢትዮጵያ ለማብቀል አልታለመም ነበር። ሆኖም ግን አንዳንድ የአብዮቱ ባላንጣዎች ከስሙ ጀምረው አብዮታዊ እንቅስቃሴውን ሕዝባዊነት በመካድ፤ ተማሪ ያመጣው ጣጣ፣ እርስ በርሱ የተገዳደለ ትውልድ የሚሉ አምታች ቃላትን መደጋገም አዋቂነት ይመስላቸዋል። የቤት ለቤት አሰሳ ሲታወስ የሚያማቸው፣ ነፃ እርምጃ ሲተረክ እንቅልፍ የሚነሳቸው፣ ቀይ ሽብር ሲነሳ የሚነዝራቸው፤ የየካቲት ሕዝባዊ አብዮት አመጣጡን፣ ሂደቱን፣ ውጤቱን ከመተንተን ይልቅ ትውልዱ ላይ የሚያሰሙትን አሉባልታና ዘለፋ በዚህ እትማችን ማንሳታችን መጥቀሙ አይቀርም ብለን እናምናለን።

የየካቲት 1966 ዓ.ም. 48ኛ ዓመትን ስንዘክር በወቅቱ ለጋ ቢሆኑም ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን ከተላበሱ ድርጅቶች የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) እና የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) አብይ ተጠቃሾች ናቸው። ይሁንና ሁለቱም የፖለቲካ ድርጅቶች የየካቲትን ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የወለዱና ያመጡ አይደሉም። የዛሬ 48 ዓመቱ የካቲት 1966 ዓ.ም. እንቅስቃሴ በመምህራኑ፣ በታክሲ ነጂዎች፣ በተማሪዎች፣ በሠራዊቱ፣ በእምነት ተቋማት፣ በሴቶች፣ በአፈር ገፊው ገበሬ፣ በላብ አደሩና በሠራተኛው በጥቅሉ በአሥራ አራቱም ክፍለ ሀገራት ነዋሪዎች ተሳትፎ የተቀጣጠለ፤ በርግጥ አቅጣጫውን ቢስትም ነገር ግን የሥርዓት ለውጥ ያመጣ ሁሌም ሊዘከር የሚገባው ሕዝባዊ አብዮት ነው።

የየካቲት 1966 ዓ.ም. አብዮትን ተገን አድርጎ ለሥልጣን የበቃው ደርግ ውስጥ የበቀለው ገዳይና ፋሽስት መንግሥቱ ኃይለማርያም ትውልድን ጭጭ ያደረገና የገዛ ቢሆንም ያ ትውልድ እና የካቲት አብዮት ሊወገዙ አይገባም። ቀደም ሲል የተፈለፈሉ የፖለቲካ ድርጅቶች የካቲት 1966 ዓ.ም. እቅስቃሴ የፈጠረላቸውን አጋጣሚ ተገን አድርገው ኖረው፤ በሁዋላም ጊዜና ወቅት ለነሱ አድልቶ ሲገኝ ዛሬ ሀገራችንን እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ በዘርና ቋንቋ ከፋፍለው ቀጥሎም በከፋ መልኩ የዘር ማጥፋት ደረጃ በመዝፈቃቸው የያ ትውልድና የካቲት 1966 አብዮት ሊወገዙ አይገባም። ትላንት በሠራነው ስህተት እና በጎ ጎን የያ ትውልድ የራሱ ድርሻ ቢኖረውም እንቅልፍ የሚነሳንን የቀይ ሽብር ወንጀል ለማካካስ ስንል የካቲት 1966ን ማጠልሸትና ታሪኩን ማጣመም አግባብ እንዳልሆነ አድምቀን እናሰምርበታለን።

የየካቲት 1966 ዓ.ም. ሕዝባዊ አብዮት ያመላከታቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች ዛሬም በሀገራችን ምላሽ አላገኙምና ከፍ ብለው የሚውለበለቡ ናቸው። "የዴሞክራሲያ መብት ያለገደብ" ፤ ሕዝብ የራሴ

**በራሴ ያለው የሕዝብ መንግሥት ይቋቋም፤ ያለ ሕዝባሚዊ መንግስት ሰላምና ዲሞክራሲ አይኖርም፤ የሚለው ጉዳይ ዛሬም የመፈክሮች ቁንጮ መሆኑን የካቲት** 1966 **እንቅስቃሴ ያስተምረናል። የዘርና የቋንቋ አከላለል ተወግዶ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜት ያብብ ዘንድ በአንድ ሕዝባዊ መፈክር፣ ያለ ዘር፣ ፆታና ሃይማኖት ልዩነት በአሥራ አራቱም ክፍለ ሀገራት የተቀጣጠለው የየካቲት** 1966 **ዓ.ም.** **ሕዝባዊ አብዮት ልንማርበት ፈቃደኛ ከሆንን ዛሬ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከተዘፈቀችበት ዘግናኝ የዘር ፍጅት አውጥቶን የሀገራችንን ዳግም ትንሳዔ ለማየት እንዲያበቃንና እንደ የካቲቱ የተኮላሸ አብዮት ሳይሆን የሠመረ ሕዝባዊ ሥልጣን ለኢትዮጵያ ተፈጥሮ የምናይበት ጊዜ እሩቅ እንዳይሆን እንመኛለን።**

**የካቲት ለኢትዮጵያችን ዳግም ልደት**!!!
**ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይጠብቅ**!!!
**የያ ትውልድ ታሪክ ህያው ነው**!!!
**ያ ትውልድ ተቋም የካቲት** 11 **ቀን** 2014 **ዓ.ም**. (February 18, 2022)

Email : yatewlid@gmail.com
website : http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org
Facebook:- Yatewlid